# የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር

## በጊዚያዊ የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ የአቋም መግለጫ

ሜይ 6 ቀን 2006 ዓ/ም በጀርመን ፍራንክፈርት የተጠራውን ህዝባዊ ስብሰባ መሰረት በማድረግ ከተለያዩ የሰሜን አሜሪካና አውሮፓ ተወክለው የመጡ የድርጅቱ አባሎች ለሁለት ተከታታይ ቀናቶች ስብሰባ በማድረግ የኢ.ህ.አ.ግ.ን  የትግል አቅጣጫ አስመልክቶ ሰፊ ውይይት በማድረግ የአቋም መግለጫ ለማውጣት ውሳኔ ላይ ደርሷል፡፡

እንደሚታወቀውና እንደታየው የግንቦት 97 ምርጫ የህዝባችን የህግ ተገዥነቱን፣ ስልጡንነቱንና የዴሞክራሲያዊ ስርዐት መስፈን አስፈላጊነቱን በውጭ ለምንገኝ ኢትዮጵያውያኖችና ለአለም ዓቀፍ ህብረተሰብ በተግባር ቢያረጋግጥም እነሆ በ12 ወራት በታየው ሂደት ግልጽ የሆነው ነገር በሃገራችን ህግና ፍትህ ትርጉም አጥቶ የዴሞክራሲ ጭላንጭል ተዳፍኖ ህዝባችን በጭካኔና በአረመናዊነት ወደወያኔ ማጎሪያ እየተጋዘና እየተጨፈጨፈ ይገኛል፡፡ በቅርቡም እንደሰማነው የተለያዩ የውጭ አገር አምባሳደሮችና ድፕሎማቶች የዚሁ አፈናና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አጋርነታቸውን በአደባባይ ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

ብዙዎቻችን በወያኔ አጀንዳ ዙርያ ከመሽከርከር ወጥተን ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ወደአንድ ሊያመጣ የሚያስችል ራዕይና አደረጃጀት መሠረት በማድረግ ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ጋር በመቆም በቁርጠኝነትና በፍጥነት የወያኔን እድሜ ማሳጠር ይጠበቅብናል፡፡ ይህን እውን ለማድረግ የሚቻልበትን መንገድ ኮሚቴው በስፋት ከተወያየ በኋላ የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅድ አውጥቷል፡፡ ጉባኤው በዕለቱ በዋንኛነት ያያቸው ነጥቦች እንደሚከተሉት ናቸው

1. የኢ.ህ.አ.ግ. ራዕይ ምን መሆን አለበት ለሚለው ከለንደን ቆራጥ የቀረበውን የረቂቅ ሰነድ ከመረመረና ካጤነ በኋላ በሁለት መሰረታዊ ነጥቦች ስምምነት ላይ ደርሷል፡፡

ሀ. የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር በራሱ ለማንም የፖለቲካ ድርጅት ያልወከለና የራሱ የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ የሌለው ሃገሪቷን ነጻ እንድትሆን መስዋትነት የሚከፍል አርበኛና ህገመንግስታዊ ጦር እንዲሆን ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

ለ. ከላይ የተጠቀሰውን ራዕይ መሠረት ያደረገ በአገር ውስጥና በውጭ የፖለቲካ ድርጅቶችና አገር ወዳዶችን ሁሉ ያካተተ ጊዚያዊ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም የሚል አገራዊ ጥሪን የሚያቀርብ ነጥብ ሰነዱ እንዲያካትት ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

ከላይ በቁጥር 1 ሀ እና ለ የተጠቀሱትን 2 መሠረታዊ ነጥቦች ያካተተው ሰነድ በአለም አቀፍ የኢ.ህ.አ.ግ. ድጋፍ ኮሚቴ ስም ለግንባሩ በቅርቡ እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አይቶና መርምሮ ሲያፀድቀው ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የኢ.ህ.አ.ግ. ራዕይን ይፋ እንደሚያደርግ ከወዲሁ መግለፅ እንወዳለን፡፡

2. ከሰሜን አሜሪካ የቀረበውን የአደረጃጀትና ህገ ደንብ ረቂቅ ከመረመረና ከተወያየ በኋላ የቀረቡትን ማሻሻያና ማስተካከያ መሠረት ያደረገ ረቂቅ እንዲቀርብና ይህንኑ መሠረት ያደረገ አደረጃጀት በመከተል ኮሚቴው

ያልተቋቋመባቸውን አገሮች በፍጥነት አዋቅሮ በ6ወር ጊዜ ውስጥ የያገሩን ተወካዮች ያካተተ ኮንፍራንስ በማድረግ አሁን ያለውን የአለምአቀፍ ጊዚያዊ ኮሚቴ በቋሚ አመራር ኮሚቴ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመተካት ውሳኔ ላይ ደርሷል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በጥልቀት ለመመርመርና ለማየት በተቻለበት በዚህ ጉባኤ ኮሚቴው የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታና የህዝባችንን ሰቆቃ በመኮነን የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥቷል፡-

1. በአገራችን እየተቀጣጠለ ያለው ሁለገብ የነፃነት የአገርና የህዝባችንን የማዳን ትግል በተፋፋመ መንገድ እንዲቀጥል በትግል ላይ የሚገኘው ህዝባችን ብቻውን አለመሆኑን ተገንዝቦ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር (ኢ.ሕ.አ.ግ) ጎን ሆኖ በመሰለፍ የነፃነት ትግሉን እንዲያፋፍም ጥሪ እናቀርባለን።
2. በውጭ አገር በስደት የምንኖር ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በዘር፣ በሐይማኖት፣ በሞያና በፖለቲካ አመለካከት ሳንለያይ አንድ ሆነን «ሃገርንና ወገንን» ለማዳን በሚደረገው ትግል በሙሉ አቅም በመሳተፍ ለወገናችን የይድረስልኝ ጥያቄ መልስ ለመስጠት በቁርጠኝነት መነሳታችንን እናረጋግጣለን።
3. በተለያዩ አላማዎችና ፕሮግራሞች በመሳርያም ሆነ በሰላማዊ መንገድ ህገወጡና ፋሺሽቱን የወያኔ ኢህአደግ መንግስት በመታገል ላይ የሚገኙ ግንባሮችና የፖለቲካ ድርጅቶች ወቅቱ «ሃገርንና ወገንን የማዳንና የነፃነት ትግል» ጊዜ መሆኑን ተገንዝበው ልዩነታቸውን በማጥበብ ከግል ፍላጎት ይልቅ ብሔራዊ ጥቅምን ያስቀደመ አንድ ታላቅ ፀረ ወያኔ የትግል ግንባር መፍጠር፣ የህዝባችንን ሰቆቃና የመከራ ገመድ ለማሳጠር ቅድሚያ በመስጠት እንዲቀሳቀሱ የኢ.ህ.አ.ግ. ጊዚያዊ አለም አቀፍ ኮሚቴ አገራዊ ጥሪ እያቀረበ ለተግባራዊነቱ ያለሰለሰ ጥረት ለማድረግ ቃል ይገባል።
4. በፀረ ወያኔ የትግል ጎራ አለን የሚሉ ግንባሮችና የፖለቲካ ድርጅቶች ለትግሉ የሚያበረክቱት የሚታይና የሚጨበጥ ነገር ካለ በድርጊታቸው ለህዝብ ከማሳየትና አልፊው በትግሉ ጎራ በተጨባጭ በመዋደቅ ላይ የሚገኙትን ግንባሮችና የፖለቲካ ድርጅቶች ስም ማጥፋት በሃሰት ወሬ ውዥንብር መፍጠር ትግሉን እጅግ የሚጎዳ መሆኑን አውቀው ከዚህ ተግባራቸው እንዲቆጠቡና እርስ በእርስ በመጠላለፍና ለጠላት መሣርያ ከመሆን ይልቅ የሁላችንም የትግል አቅጣጫ አላማ ወያኔ እንዲሆን እየጠየቅን ህዝባችንም ለዚህ ነቅቶ እንዲታገል በዚህ አጋጣሚ ጥሪ እናደርጋለን።
5. በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የህዝባቸውን ሰቆቃና እልቂት ለጊዚያዊ ጥቅማቸውና ሆዳቸው የሸጡ ተለጣፊ ባንዳዎች አገርና ህዝብ የማያልፍና የማይጠፋ አምባገነኖችና ጨፍጫፊዎች ግን የሚያልፉና የሚጠፉ መሆናቸውን ተገንዝበው ከዚህ እኩይ ተግባራቸው ተቆጥበው ሕዝቡን ይቅርታ በመጠየቅ ትግሉ ጎራ እንዲቀላቀሉ ጥሪ እናቀርብላቸዋለን።
6. ከሕዝብ አብራክ የወጡ ነገር ግን የጨፍጫፊና ህገወጥ መንግስት እንባ ጠባቂ ሆነው የሚገኙት የፀጥታ፣ የፌደራል ፖሊስና የጦር አባሎች ሁሉ ከትናንቱ ታሪክ በመማር ከማያልፈውና ከማይጠፋው አገርና ህዝብ ጎን እንዲሠለፉ ጥሪ እናቀርብላቸዋለን።
7. የህዝባችንን ጩኸት፣ ብሶትና እልቂት እያዩ እንዳላዩ እየሰሙ ጆሮአቸውን የደፈኑ መንግሥታት በእነሱ የገንዘብና ወታደራዊ ድጋፍ ሕዝባችን እየተጨፈጨፈ መሆኑን ተረድተው ህገወጡንና ፋሺሽቱን የወያኔ መንግስት ከመደገፍና ከመርዳት እንዲቆጠቡ እየጠየቅን ለዘለቄታዊ ጥቅምና ትብብር ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን እንዲሰለፉ በአክብሮት እንጠይቃለን። ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን እስከዛሬ ለፈሰሰው ደምና ለወደፊቱም በሕዝባችን ለሚፈጸመው ሰቆቃ በታሪክ ተጠያቂ መሆናቸውን እንዲታወቅ እናስገነዝባቸዋለን።
8. በመጨረሻም በአገር ውስጥ በአርበኝነት ለነፃነታቸውና ለአገራቸው መሰዋትነት ለከፈሉትና በመክፈል ላይ ለሚገኙት ውድ ወገኖቻችን ያለንን ከፍተኛ አድናቆትና ክብር የትግል አድነታችን በሙሉ ልብ

እናረጋግጥላቸዋለን። እንዲሁም በችግራችን ወቅት ከጎናችን በመሰለፍ ድጋፍ ለሚሰጡን የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጆችና መንግስታት ታላቅ ምስጋና እናቀርባለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ**
**ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ መስዋትነት አንድነቷና ነፃነቷን ጠብቃ ለዘላለም ትኖራለች**

**ሜይ 6 2006**
**ፍራንክፈርት ጀርመን።**